የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሪዲቴሽን ጽ/ቤት
# የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ
# ኦዲት ሪፖርት

ታህሳስ 2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሪዲቴሽን ጽ/ቤት

## የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ

## ኦዲት ሪፖርት

የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሪዲቴሽ ጽ/ቤት የተመደበለትን በጀት በፋይናንስ አዋጅ፣ደንብ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሠረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሃብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2011 በጀት ዓመት የሂሣብ ሪፖርቶች እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የጽ/ቤቱ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተርን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ/የኦዲት አስተያየት/ ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ጽ/ቤቱ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በጽ/ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የጽ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት
- የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ሪፖርት
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት
- የሂሣብ ማመዛዘኛ ሪፖርት
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት

የጽ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት በትክክል የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ደንብ መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

**የወጪ ሂሳብ**

1. የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ የተፈጸመ የትራንስፖርት ክፍያ በድምሩ ብር 14,292.00 ተገኝቷል፡፡
2. ጽ/ቤቱ የህትመትና የፋይል አቃፊ ግዥ ሲፈጽም የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይቀርብለት በወጪ ማስመስከሪያ 445226 ብር 21,000.00 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል ፡፡

ከላይ ከተገለጹት በስተቀር በእኛ አስተያየት የጽ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30/2011 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውን ገቢ፣ የተከፈለውን ወጪና የበጀት አጠቃቀሙን በአጥጋቢ ሁኔታ ያሳያሉ፡፡

**ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች**

3. ለመደበኛ ወጪ ለየፕሮግራሞቹ ከተፈቀደው በጀት ውስጥ ብር 2,724,586.51 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት መሆኑ ታውቋል፡፡
4. **የንብረት አያያዝና አስተዳደር በተመለከተ**
   - የቋሚ እቃዎች ቆጠራ ቅጽ ላይ የቋሚ ዕቃው መለያ ቁጥር ያልተገለጸ መሆኑ፤
   - በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ የንብረት ቆጠራ ቢደረግም ተመዛዝኖ ከወጪ ቀሪ ያልተረጋገጠ መሆኑን ታውቋል፡፡
   - አገልግሎት የማይሰጡ 2 Dell ,5 HP , 4 toshipa and 1 Nenova በድምሩ 12 ላፕቶፕ በንብረት ክፍል ውስጥ ተደራርቦ ተቀምጦ መገኘቱ ታውቋል፡፡
   - የቋሚ ንብረት በሞዴል 19 ሲገባም ሆነ በሞዴል 22 ሲወጣ የተመረተበት የፋብሪካ ቁጥር (ሴሪ ቁጥር) ያለመመዝገቡ፣

5. **<u>የውስጥ ኦዲት ሪፖርትን በተመለከተ</u>**

- የውስጥ ኦዲት ሪፖርት የ2ኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት እና የ4ኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት በውስጥ ኦዲት መመሪያ የኦዲት ማቅረቢያ የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ያልቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡

6. በ6 የወጪ ማስመስከሪያዎች በጀት ስለመኖሩ ያረጋገጠው፣ የሂሳቡን ትክክለኛነት እና ወጪውን ያዘዘው ቦታ ላይ በፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክተሩ ተፈርሞ ብር 190,933.50 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

7. የጽ/ቤቱ የዓመታዊ የግዥ ዕቅድ ሲዘጋጅ በግዥ አፈጻጸም መመሪያ መሠረት የግዥ ዕቅድ ይዘትን ተከትሎ ያልተዘጋጀ መሆኑ ታውቋል፡፡

ከሠላምታ ጋር

------------------------

አንድነት ብዙሰው

የኦዲት ሥራ አስኪያጅ

ቀን :27/4/12